# Merion School
## ሜሪዮን ት/ቤት

**Address – Yeka Abado, Gedera, next to Wereda 14 Health Center**
**E- Mail**merionschool2@gmail.com


ስም _____ **2015** ዓ.ም ክፍል፡-**8**ኛ
ቀን_____**3**ኛው ተርም የክለሳ ጥያቄ **1** የት/ት ዓይነት፡- አማርኛ

**ትዕዛዝ አንድ፡- ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛ መልስ ምረጡ።**

_____1. ተዋኒያን የሌሎችን ሰዎች ባህሪይ ወርሰው ከቋንቋ ጋር በማወዳደር መድረክ ላይ የሚያቀርቡት የስነ- ጽሑፍ ዘርፍ ምን ይባላል?
ሀ. ስነ-ቃል ለ. ግጥም ሐ. ተውኔት መ. ልቦለድ

_____2. ከሚከተሉት ውስጥ አንዱ የተውኔት ሙያዊ ቃል ነው?
ሀ. ገቢር ለ. ጎንታ ሐ. ትልም መ. ሀ እና ለ

_____3. በተዋኒያን መካከል የሚደረግ የንግግር ቅብብሎሽ _____ ይባላል።
ሀ. ታሪክ ለ. ቃለ ተውኔት ሐ. ትዕይንት መ. ገቢር

_____4. ‹‹መዋተት›› ለሚለው ቃል ፍቺ ሊሆን የሚችለው የቱ ነው?
ሀ. መቀመጥ ለ. ዕረፍት ሐ. መባከን መ. ሀ እና ለ

_____5. ሕፃኑ የፈለገው ነገር ስለተሟላለት በደስታ _____። በባዶ ቦታው የሚገባው ቃል፡-
ሀ. ዘለለ ለ. ቦረቀ ሐ. አማረ መ. ሀ እና ለ

_____6. ምፀትን፤ ማሾፍን እና ማሽሟጠጥን ለመግለፅ የምንጠቀመው ስርዓተ ነጥብ የቱ ነው?
ሀ. ትምህረት አንክሮ ለ. ትምህርተ ሰላቅ ሐ. ቃል አጋኖ መ. ሀ እና ለ

_____7. ቀዩ i በጣም አምሮብሃል። የዚህ ዓ.ነገር ትርጉም፡-
ሀ. ቀይ የሆነ ልጅ ሐ. ወፍራም የሆነ ልጅ
ለ. ጥቁር የሆነ ልጅ መ. መልስ የለም

_____8. ነገሮችን አግዝፎ እና አሳንሶ የሚያቀርብ ዓ.ነገር _____ ይባላል።
ሀ. አጋናኝ ዓ.ነገር ለ. ሐተታዊ ዓ.ነገር ሐ. ትዕዛዛዊ ዓ.ነገር መ. መጠይቃዊ ዓ.ነገር

_____9. ቤቱን አፅዱ! ይህ ዓ.ነገር ከየትኛው የዓ.ነገር አይነት ይመደባል።
ሀ. ሐተታዊ ለ. አጋናኝ ሐ. መጠይቃዊ መ. ትዕዛዛዊ

_____10. ‹‹ልል›› ለሚለው ቃል ተቃራኒ ፍቺ የሆነው የቱ ነው?
ሀ. ጥብቅ ለ. የላላ ሐ. የተፈታ መ. ሀ እና ለ

_____11. ሰውየው ሁለት ምላስ ነው።የተሰመረበት ቃል ፍቺ፡-
ሀ. ሀቀኛ ለ. ሁለት ምላስ ያለው ሐ. ውሸታም መ. እውነተኛ

_____12. ከሚከተሉት አማራጮች ውስጥ የተለየ ትርጉም የሚሰጠው የቱ ነው?
ሀ. ቢወቅጡት እንቦጭ ለ. ከርሞ ጥጃ ሐ. አድሮ ቃሪያ መ. ሆድና ጀርባ

_____13. እኩይ ለሚለው ቃል ተቃራኒ ፍቺ የቱ ነው?
ሀ. አስቸጋሪ ለ. መጥፎ ሐ. ሰናይ መ. ሀ እና ለ

_____14. ስውር ለሚለው ቃል ተመሳሳይ ፍቺ የሆነው የቱ ነው?
ሀ. ግልፅ ለ. የሚታይ ሐ. ህብዕ መ. ያልተደበቀ

_____15. ባህር ለሚለው ቃል ፍካሪያዊ ፍቺ የሆነው ቃል፡-
ሀ. የተኛ ውሃ ለ. ሰፊ ሐ. የውሃ ክፍል መ. ጠባብ

_____16. መሬት ለሚለው ቃል እማሪያዊ ፍቺ ሊሆን የሚችለው፡-
ሀ. ቻይ ለ. የሰዎች መኖሪያ ሐ. ደረቅ መ. ሀ እና ለ

_____17. ለሆሳስ ለሚለው ቃል ፍቺ፡-
ሀ. ጩኸት ለ. ሁከት ሐ. ሹክሹክታ መ. ሀ እና ለ

_____18. የልቦለድ ታሪክ የተፈፀመበትን ጊዜና ቦታ የሚያመለክት የቱ ነው?
ሀ. ሴራ ለ. ትልም ሐ. መቼት መ. ግጭት

_____19. ከሚከተሉት ውስጥ የአጭር ልቦለድ ባህሪይ ያልሆነው የቱ ነው?
ሀ. ነጠላ ውጤት ለ. ቁጥብነት ሐ. እምቅነት መ. ጥድፊያ

_____20. ከሚከተሉት ውስጥ ኢ-ልቦለድ ያልሆነው የቱ ነው?
ሀ. ደብዳቤ ለ. የሕይወት ታሪክ ሐ. ዘገባ መ. ተውኔት

¾¨LÏ / ¾›dÇÑ> eU_____ò`T_____k”_____

MERION SCHOOL